የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጉምሩክ ኮሚሽን
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቁጥር/ Ref.No. 4/08/3/14
ቀን/Date መስከረም 26 2014

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ
<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>የተመረጡ የኢኮኖሚ እንቀሳቃሾች ፕሮግራም አሠራር ስለመላክ፤</u>

በተቋሙ ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ የተመረጡ የኢኮኖሚ እንቀሳቃሾች ፕሮግራም ተግባራዊ እየተደረገ ቢሆንም በፕሮግራሙ አፈጻጸም ላይ ግልጽነት ያልነበረው በመሆኑ አገልግሎቱ ግልጽነት ባለው መልኩ ለመተግበር እንዲቻል "የተመረጡ የኢኮኖሚ እንቀሳቃሾች ፕሮግራም አሠራር" ተዘጋጅቷል፡፡

በመሆኑም የተመረጡ የኢኮኖሚ እንቀሳቃሾች ፕሮግራም በተዘጋጀው የአሠራር ስርዓት መሠረት በጥብቅ ዲሲፕሊን ተፈጻሚ እንዲደረግ እያሳሰብኩ፤ የደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት የፀደቀውን የተመረጡ የኢኮኖሚ እንቀሳቃሾች ፕሮግራም ሰነድ በኮሚሽኑ ዌብሳይት እና ኮሚሽኑ በሚጠቀምባቸው ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች ለተገልጋዮች ተደራሽ እንዲያደርግ እየገለጽኩ፤ የሰነዱን ቅጅ 29 ገጽ አባሪ በማድረግ የተላከ መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

<u>ግልባጭ፤</u>
- ለኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ዘርፍ
  <u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>



ስልክ/Tel:- +251 116 67 54 58
:- +251 116 62 98 19
ፖ.ሳ.ቁ. 2559
Email: hocrecordopr@gmail.com
Website:- www.ecc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

- ለስትራቴጂክ ፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለስትራቴጂክ አጋርነት ዳይሬክቶሬት
- ለውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት
- ለተቋም አቀፍ ሥጋት ሥራ አመራርና ሥነ-ምግባር ዳይሬክቶሬት
- ለትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለገቢ ዕቃ አወጣጥ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለአምራችና ወጪ ንግድ አሠራና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለዋጋ ትመናና ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለታሪፍና ሥሪት ሀገር አወሳሰን ዳይሬክቶሬት
- ለህግ ተገዥነትና ሥጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት
- ለድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

<u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>፣

- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞጆ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅግጅጋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሀዋሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞያሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዋሽ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሠመራ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጋላፊ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአሶሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመቀሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅቡቲ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
- ለታጁራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

<u>በያሉበት</u>፣

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ጉምሩክ ኮሚሽን
F.D.R.E. CUSTOMS COMMISSION
የውስጥ መገናኛ
INTERNAL OFFICE MEMORANDUM

ጉምሩክ ኮሚሽን
CUSTOMS COMMISSION

ቁጥር፡ ጉኦዘ/6/494/14

ለ፡ ክቡር የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

ከ፡ ጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ

ቀን፡ 19/1/2014 ዓ.ም.

ጉዳዩ፡- የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም የጥናት ሰነድን ይመለከታል፤

ተቋሙ ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም ተግባራዊ እያደረገ ቢሆንም ግልፅ አሰራር ባለመኖሩ ነባሩ ጥናት የተወሰነ ማስተካከያ ተደርጎበት በማሻሻል እንዲፀድቅ ቀርቦ ግብረመልስ የተሰጠበት ሲሆን በተሰጠው ግብዓት መሰረት የተስተካከለውን ሰነድ ፀድቆ ተግባራዊ እንዲሆን የንግድ ገቢ ዕቃ አወጣጥ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት በቀን 18/1/2014 ዓ.ም. በቁጥር ዕቃ/90/2014 በተፃፈ የውስጥ ማስታወሻ የተዘጋጀውን ሰነድ 29 ገጽ አባሪ አያይዞ አቅርቧል፡፡

በዚሁ መሠረት ዝርዝር ውይይት ተደርጎበት እና ግብዓት ተሰብስቦበት የተዘጋጀው ረቂቅ የአሰራር ማንዋል ፀድቆ ስራ ላይ እንዲውል ውሳኔ እንዲሰጥበት 29 ገጽ አባሪ አያይዘን ለውሳኔ አቅርበናል፡፡

ግልባጭ/

- ለንግድ ገቢ ዕቃ አወጣጥ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት /ያለአባሪ/

ጉምሩክ ኮሚሽን

Ethiopia Customs Commission
Records Documentation
No.1

ጉምሩክ ኮሚሽን
CUSTOMS COMMISSION

# የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን

---

## የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም
## የአሰራር ማንዋል

ሰኔ 2013
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

## መግቢያ

ለንግድ እንቅስቃሴ ቅልጥፍና ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የስጋት ስራ አመራር መርህን የተከተለ ለተገልጋዩ ፍትሐዊ፤ ፈጣን፤ ተገማች እና አመኔታን ያተረፈ የጉምሩክ አገልግሎት መስጠት፤ የአምራች ኢንዱስትሪውና የኢኮኖሚ ልማትን መደገፍ፤ አስመጪዎችና ላኪዎች በራሳቸው አነሳሽነት የዕቃዎችን ዋጋ እንዲሁም የቀረጥና ታክስ ስሌት መግለጫ በማቅረብ የሚከፍሉበትን ስርዓት ማጎልበት የሚያስፈልግ መሆኑ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 በአሰራር መርህዎች ክፍል ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ይህንኑ በሚገባ ለመደገፍ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ በአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ የሚሳተፉ አስመጪዎችና ላኪዎች እንዲሁም የዕቃና የጉምሩክ አስተላላፊዎች ተለይተው በተቀመጡ መስፈርቶች እየተመዘኑ በተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም እንዲታቀፉ በማድረግ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እየተደረጉ የቆዩ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ይሁንና ሲሰራበት የቆየው የአሰራር ስርዓት ሳይሆን የጥናት ሰነድ በመሆኑና ይህም ሰነድ በአግባቡ ሊያሰራ የሚያስችል ባለመሆኑ እንዲሁም የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ድርጅቶች ሊከተሉት የሚገባዉን ስርዓት በግልፅ ያላስቀመጠ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ስለሆነም በተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም በአቅርቦት ሰንሰለቱ ተዋናዮች ግልጽ መስፈርት ማስቀመጥ በማስፈለጉ፤ በፕሮግራሙ የሚታቀፉ ድርጅቶች ሊደረግላቸው የሚገባውን ድጋፍ ለማጠናከር፤ ለፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች በሁሉም የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ወጥነት ያለውና ግልጽ አገልግሎት ለመስጠት እና በቀጣይ ለሚጣቀፉ መብትና ግዴታቸውን እንዲያውቁ ትምህርትና ስልጠና በመስጠት ፕሮግራሙን ለማስፋት እንዲሁም በሚደረግ የድጋፍና ክትትል ስራ ስለሚወሰድ የማስተካካያ እርምጃ በግልጽ ማስቀመጥ በማስፈለጉ ይህ የአሰራር ማንዋል ተዘጋጅቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## 1. ትርጓሜ

ለዚህ አሰራር ሲባል ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ቃላት/ሀረጎች ፍቺ ተሰጥቷቸዋል፡፡

1.1 **"የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ፕሮግራም"** ማለት በአለም አቀፍ ገበያ የአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ድርጅቶች ኮሚሽኑ ባስቀመጣቸው መስፈርቶች ተመዝነው ማሟላታቸው ሲረጋገጥ የሚታቀፉበት ስርዓት ነው፡፡

1.2 **"የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ"** ማለት በሀገሪቷ ህግ ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ በንግድ፣ በኢንቨስትመንት፣ በዕቃ አስተላላፊነት እና በጉምሩክ አስተላላፊነት እንቅስቃሴ ውስጥ የሚሳተፍ ሰው ወይም ድርጅት ነው፡፡

1.3 **"የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ"** ማለት በዓለም አቀፍ ንግድ አቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተሳታፊ የሆነና በኮሚሽኑ የተዘጋጁ መስፈርቶችን በማሟላት በተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ፕሮግራም የታቀፈ ድርጅት ነው፡፡

1.4 **"ቅድመ ኦዲት"** ማለት በተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ፕሮግራም ለመታቀፍ የሚያመለክቱ ድርጅቶች በኮሚሽኑ ኦዲት ከመደረጋቸው በፊት በተዘጋጀ መስፈርት መሰረት ራሳቸውን መዝነው የሚያቀርቡበት ሂደት ነው፡፡

1.5 **"የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ የአሰራርና የህግ ተገዥነት ኦዲት"** (AEO Compliance and system audit) ማለት በአቅርቦት ሰንሰለት ተሳታፊ የሆኑ ድርጅቶች በተዘጋጀ የህግ ተገዥነትና የውስጥ አሰራር መስፈርት ተመዝነው ለፕሮግራሙ ብቁ መሆናቸዉን እና አለመሆናቸዉን ለማረጋገጥ የሚከናወን የኦዲት ሂደት ነው፡፡

1.6 **"የአቅርቦት ሰንሰለት"** ማለት በዕቃ አምራች ወይም አቅራቢ እና ገዥ ወይም ተጠቃሚ መካከል የሚደረግ የዕቃ ቅብብሎሽ ሂደት ነው፡፡

1.7 **"አምራች"** ማለት ጥሬ እቃዎችን፣ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ተበትነው የሚመጡ እቃዎችን ከውጭ ሃገር በማስመጣት ወይም የሃገር ውስጥ ጥሬ ዕቃን በመጠቀም በሃገር ውስጥ ተጨማሪ እሴት በሚፈጥር ማንኛውም ምርት የማምረት ወይም የመገጣጠም ሥራ ዘርፍ ላይ የተሰማራ፤ ለሃገር ውስጥ ፍጆታ ወይም ለውጭ ንግድ ዓላማ የሚያመርት ድርጅት ነው፡፡

1.8 **"አስመጪ"** ማለት እቃ ከውጭ ሃገር አስመጥቶ ለሃገር ውስጥ ገበያ የሚያቀርብ ድርጅት ነው፡፡

1.9 **"ላኪ"** ማለት ዕቃን ከሀገር ውስጥ ወደ ውጪ በመላክ የውጪ ምንዛሬ የሚያገኝ ድርጅት ነው::

1.10 **"የእቃ አስተላላፊ"** ማለት በኢትዮጵያ የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የዕቃ አስተላላፊነት ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ወይም ሰው ነው::

1.11 **"የጉምሩክ አስተላላፊ"** ማለት በኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል ተወስኖ ዕቃዎችን ወደ ሀገር ለማስገባት ወይም ከሀገር ለማስወጣት አስመጭ ወይም የላኪ ሰነዶችን የጉምሩክ ስነ-ስርዓት የማስፈጸም ተግባር ለማከናወን የሚያስችል የውክልና ስልጣን የተሰጠው ሰው ነው::

1.12 **"መካከለኛ የስጋት ደረጃ"** ማለት ከስጋት እና ህግ ተገዥነት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በተተነተነ መረጃ መሰረት የስጋት ደረጃው ቢጫ የሆነ ነው::

1.13 **"ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ"** ማለት ከስጋት እና ህግ ተገዥነት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በተተነተነ መረጃ መሰረት የስጋት ደረጃው አረንጓዴ የሆነ ነው::

1.14 **"በአቅርቦት ሰንሰለት ቀጥተኛ ተሳትፎ ያለው"** ማለት ዕቃ ወደ አገር በማስገባትና ወደ ውጪ በመላክ የሚሳተፍ አስመጪ፣ ላኪ፣ አስመጪና ላኪ ወይም አምራችና ላኪ ነው::

1.15 **"ኮሚሽን"** ማለት የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ነው::

1.16 **"ኮሚሽነር"** ማለት የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር ነው::

1.17 በዚህ ማንዋል ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላቶች በሌሎች የጉምሩክ ህጎች ያላቸውን ትርጉም ይይዛሉ::

## ክፍል ሁለት

## 2. የተፈፃሚነት መሰንና የማኑዋሉ ዓላማ

### 2.1 የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ማንዋል በተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም ለመታቀፍ ለኮሚሽኑ ጥያቄ በሚያቀርቡ ድርጅቶች እና በኦዲት መስፈርቶች አልፈው በፕሮግራሙ የታቀፉ ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::



ቁጥር 1
No.1
Ethiopia Customs Commission

## 2.2 የማንዋሉ ዓላማ

በተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች አሰራርና ህግ ተገዥነት ኦዲት አልፈው የፕሮግራሙ ተጠቃሚ የሆኑ ድርጅቶችን ወጥ፣ ግልፅ እና ተቀባይነት ባለው ሁኔታ ለመደገፍ እና በየደረጃው ለሚገኝ አመራርና ፈፃሚ ለአፈፃፀም ቀላልና ግልፅ የሆነ አሰራር እንዲኖር ለማድረግ ነው፡፡

# ክፍል ሶስት

# 3. የፕሮግራሙ ኦፕሬሽናል ስራዎች

## 3.1 በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ማመልከት የሚችሉ አካላት

ሀ) አስመጪ፣

ለ) አምራች፣

ሐ) አስመጪና ላኪ፣

መ) ላኪ፤

ሠ) የዕቃ አስተላላፊ፤

ረ) የጉምሩክ አስተላላፊ ናቸው፡፡

## 3.2 ራስ መገምገሚያ መርህ እና ቅድመ ኦዲት መስፈርቶች

በአቅርቦት ሰንሰለት የሚሳተፉ ድርጅቶች ከኮሚሽኑ ጋር ለሚኖር የሁለትዮሽ መልካም የስራ ግንኙነት ስለሚያጠናክርና ከዚህ ግንኙነት የሚገኝ የጋራ ጥቅም ግምት ውስጥ በማስገባት በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ፍላጎት እንደሚኖር ይታመናል፡፡

በመሆኑም በተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም ለመታቀፍ የሚያመለክቱ ድርጅቶች ከአቅርቦት የንግድ ሰንሰለታቸውና ከሚከተሉት የንግድ ስራ እንቅስቃሴ አንፃር ኮሚሽኑ በሚያዘጋጀው አለም አቀፍ ደረጃው በጠበቀ መስፈርት መሰረት ራሳቸውን በቅድመ ኦዲት መስፈርት መሰረት ገምግመው መቅረብ አለባቸው፡፡ በድርጅቱ ተሞልቶ የሚቀርበው የራስ መገምገሚያ ትክክለኛና እውነተኛ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህ የራስ መገምገሚያ መረጃ ኮሚሽኑ ከድርጅቶች ጋር የሚኖረውን ግንኙነት የሚያጠናክር ከመሆኑ ሌላ የመብቱ ተጠቃሚዎችን የማረጋገጫ ኦዲት በግብዓትነት ይጠቀምበታል፡፡

### 3.3 የቅድመ ኦዲት መስፈርቶች

#### 3.3.1 ለአስመጪ፣ አምራች እና ላኪ

ሀ) የስጋት ደረጃው ቢያንስ መካከለኛ መሆን አለበት፡፡

ለ) በሁለት በጀት ዓመት የተገኘበት የጉምሩክ ኦዲት ግኝት መጠን አጠቃላይ ከከፈለው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ከ5% ያልበለጠ እንዲሁም በሃገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት የተገኘ የኦዲት ግኝት መጠን አጠቃላይ ከከፈለው የትርፍ ግብር መጠን ከ5% ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

ሐ) የድርጅቱ የፋይናንስ እና የመጋዘን አስተዳደር የስራ ክፍሎች በመረጃ ቴክኖሎጂ የተሳሰሩ መሆን አለባቸው፤

መ) የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ላይ ካልሆነ በስተቀር ያለፊው አንድ አመት ኪሳራ ላይ መሆን የለበትም፡፡

#### 3.3.2 ዕቃ አስተላላፊ እና ለጉምሩክ አስተላላፊ

ሀ) በዓመት የተመዘገበው ቀላል የጥፋት መረጃ ከአምስት መብለጥ የለበትም፣

ለ) ባለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት ዲክሌር ባደረጋቸው ሰነዶች ላይ በተደረገ ዳግም ማጣራት የተከፈለ ወይም በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የተገኘ ተጨማሪ የቀረጥና ታክስ መጠን በአማካይ ከ10% መብለጥ የለበትም፡፡

### 3.4 የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች የሚመረጡበት ሂደት

በተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም ለመታቀፍ ጥያቄ የሚያቀርብ ድርጅት የሚከተሉትን ሂደቶችን ማለፍ ይጠበቅበታል፡፡

ሀ) በፕሮግራሙ ለመታቀፍ የሚያመለክት ድርጅት የተረጋገጠ የራስ መገምገሚያ ቅፅ በመሙላት ማቅረብ አለበት፤

ለ) በአመልካች ድርጅቱ የቀረበው የራስ መገምገሚያ ቅፅ በፕሮግራሙ መመዘኛ መስፈርቶች መሰረት የአሰራር ስርዓት እና የህግ ተገዥነት ኦዲት በማድረግ በተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ፕሮግራም ለመታቀፍ ብቁ መሆኑን በኮሚሽኑ መረጋገጥ አለበት፤

## 3.5 የራስ መገምገሚያ ቅጽ ተቀባይነት የማግኘት ሂደት

ተሞልቶ የቀረበው የራስ መገምገሚያ ቅጽ ተገቢውን መረጃና መስፈርት ያሟላ ስለመሆኑ ተረጋግጦ በኮሚሽኑ ተቀባይነት ያገኛል፤ ተገቢውን መስፈርት ያላሟላ ከሆነ ምክንያቱን በመጥቀስ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ለድርጅቱ በደብዳቤ ያሳውቃል፡፡

## 3.6 ኦዲት ለማከናወን መቅረብ ያለባቸው ማስረጃዎች

ቅድመ-ኦዲቱን አልፎ የውስጥ አሰራርና የህግ ተገዥነት ኦዲት ለማድረግ የሚከተሉት ማስረጃዎች መቅረብ አለባቸው፡፡

ሀ) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ሰርተፊኬት፣ የንግድ ፍቃድ ሰርተፊኬት፣ መመስረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ (ኮፒ)፣

ለ) የድርጅቱ መዋቅር እና ፕሮፋይል፣

ሐ) ላለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት በውጪ ኦዲተሮች የተረጋገጠ የሒሳብ ሪፖርት፣

መ) የመካከለኛ ወይም የረጅም ጊዜ ዕቅድ፣

ሠ) የሒሳብ መዝገብ አያያዝ፣

ረ) የመጋዘን አስተዳደር አሰራር፣

ሰ) የፋይናንስ ፖሊሲ/ አሰራር፣

ሸ) የሰው ሀብት ፖሊሲ/ አሰራር፣

ቀ) የጥበቃና የደህንነት ፖሊሲ/ አሰራር፣

በ) የመረጃ ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት አስተዳደር ፖሊሲ/ አሰራር፣

ተ) ዋና ዋና የስራ ክፍሎች ዲፓርትመንት ናሙና የስራ መዘርዝር፣

ቸ) ለገቢ እቃዎች ዋና ዋና የአቅራቢዎቻቸው ዝርዝር፣

ነ) የድርጅቱ የቋሚ እና ኮንትራት ሰራተኞች ዝርዝር፣

ኘ) የውስጥ አሰራር ጥራት ማረጋገጫ (እንደአስፈላጊነቱ)፣

አ) የማህበራዊ አስተዋጽኦ (እንደአስፈላጊነቱ)፣

ከ) የአካባቢ ደህንነት አሰራር (እንደአስፈላጊነቱ)፣

## 3.7 የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ፕሮግራም የህግ የተገዥነትና የአሰራር ኦዲት ሂደት

የኦዲት ሂደቱ በሚከተሉት መንገዶች በሚገኝ መረጃ መሰረት ይከናወናል፡፡

ሀ) ተሞልቶ በቀረበው የራስ መገምገሚያ ቅፅ መሰረት ስለድርጅቱ የህግ ተገዥነት ሁኔታ ከሚስተናገድባቸው የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶችና ግብር ከሚከፍልበት የታክስ ማዕከል በተሰበሰበ መረጃ መሰረት ማረጋገጥ፤

ለ) በኮሚሽኑ የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ፕሮግራም የአሰራርና የህግ ተገዥነት ኦዲት ባለሙያዎች በድርጅቱ የስራ ቦታ በአካል በመገኘት የድርጅቱን የውስጥ አሰራር ስርዓት በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ብቁ የሚያደርገው መሆኑን በዝርዝር መመዘኛ መስፈርቶች መሰረት ማረጋገጥ፡፡

ሐ) ሌሎች ተጨማሪ የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም ድርጅቱ በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ብቁ የሚያደርገው መሆኑን ማረጋገጥ፤

## 3.8 የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች የህግ ተገዥነትና የአሰራር ኦዲት መመዘኛ ጥቅል መስፈርቶች

ለፕሮግራሙ ያመለከተ እና ቅድመ ኦዲቱን ያለፈ ድርጅት የአሰራርና የህግ ተገዢነት ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ጥቅል መስፈርቶች መሰረት ይመዘናል፡፡

ሀ) በጉምሩክና በሀገር ውስጥ ገቢ የህግ ተገዥነት ሁኔታ (35%)

ለ) የገቢና ወጪ ዕቃዎች ሎጅስቲክስና ሃብት አመራር ስርዓት (20%)

ሐ) የመረጃ ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማትና አጠቃቀም (15%)

መ) የፋይናንስ ቀጣይነት (10%)

ሠ) ለሃገር ኢኮኖሚ የሚያደርገው አስተዋፅኦ (10%)

ረ) የደህንነት መስፈርቶች (10%)

## 3.9 የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ፕሮግራም መመዘኛ መስፈርቶች

### ሀ) አስመጪ

1) ባለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት የተከፈለ አማካይ የቀረጥና ታክስ መጠን (6%)
2) ባለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት ተከፈለ አማካይ የግብር መጠን (6%)
3) የፈጠረው ስራ ዕድል (3%)
4) ዕዳውን ለመክፈል ያለው አቅም (4%)
5) ባለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት አማካይ የሽያጭ መጠን (3%)
6) ባለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት አማካይ የትርፍ መጠን (3%)

የኢትዮጵያ የጉምሩክ ኮሚሽን
ቁጥር 1
No.1
Ethiopia Customs Comm.
Records Documentation

7) በድህረ ዕቃ አወጣጥ የኦዲት ግኝት መጠን (8%)

8) በጉምሩክ ስነ-ስርዓት ሂደት የተከፈለ ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ መጠን (8%)

9) የወኪሉ የህግ ተገዥነት ታሪክ (4%)

10) ዓመታዊ ግብርን በወቅቱና በፈቃደኝነት አሳውቆ የመክፈል ሁኔታ (7%)

11) የሃገር ውስጥ ገቢ የኦዲት ግኝት መጠን (8%)

12) በዕቅድ የመመራት ባህል (3%)

13) የፀደቀ የአሰራር ስርዓት (6%)

14) የስልጠና አሰጣጥ ሁኔታ (3%)

15) የሰራተኛ ደህንነት ሁኔታ (3%)

16) የመረጃ ቴክኖሎጂ ደህንነት ሁኔታ (5%)

17) የመረጃ ቴክኖሎጂ ትስስር ሁኔታ (5%)

18) የመረጃ ቴክኖሎጂ የማስተዳደር ሁኔታ (5%)

19) የመረጃ አያያዝና ደህንነት ሁኔታ (4%)

20) የድርጅቱ ቅጥር ግቢና መጋዘን ደህንነት ሁኔታ (6%)

**ለ) አምራች**

1) የኢንቨስትመንት መጠን (6%)

2) ባለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት ተከፈለ አማካይ የግብር መጠን (6%)

3) የፈጠረው ስራ ዕድል (3%)

4) ዕዳውን ለመክፈል ያለው አቅም (4%)

5) ባለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት አማካይ የሽያጭ መጠን (3%)

6) ባለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት አማካይ የትርፍ መጠን (3%)

7) በድህረ ዕቃ አወጣጥ የኦዲት ግኝት መጠን (8%)

8) በጉምሩክ ስነ-ስርዓት ሂደት የተከፈለ ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ መጠን (8%)

9) የወኪሉ የህግ ተገዥነት ታሪክ (4%)

10) ዓመታዊ ግብርን በወቅቱና በፈቃደኝነት አሳውቆ የመክፈል ሁኔታ (7%)

11) የሃገር ውስጥ ገቢ የኦዲት ግኝት መጠን (8%)

12) በዕቅድ የመመራት ባህል (3%)

13) የፀደቀ የአሰራር ስርዓት (6%)

14) የስልጠና አሰጣጥ ሁኔታ (3%)

15) የሰራተኛ ደህንነት ሁኔታ (3%)

16) የመረጃ ቴክኖሎጂ ደህንነት ሁኔታ (5%)
17) የመረጃ ቴክኖሎጂ ትስስር ሁኔታ (5%)
18) የመረጃ ቴክኖሎጂ የማስተዳደር ሁኔታ (5%)
19) የመረጃ አያያዝና ደህንነት ሁኔታ (4%)
20) የድርጅቱ ቅጥር ግቢና መጋዘን ደህንነት ሁኔታ (6%)

ሐ) ላኪ

1) ባለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት ያስገኘው አማካይ የውጭ ምንዛሬ መጠን በአሜሪካ ዶላር (6%)
2) ባለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት ተከፈለ አማካይ የግብር መጠን (6%)
3) የፈጠረው ስራ ዕድል (3%)
4) ዕዳውን ለመክፈል ያለው አቅም (4%)
5) ባለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት አማካይ የሽያጭ መጠን (3%)
6) ባለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት አማካይ የትርፍ መጠን (3%)
7) በድህረ ዕቃ አወጣጥ የኦዲት ግኝት መጠን (8%)
8) በጉምሩክ ስነ-ስርዓት ሂደት የተከፈለ ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ መጠን (8%)
9) የወኪሉ የህግ ተገዥነት ታሪክ (4%)
10) ዓመታዊ ግብርን በወቅቱና በፈቃደኝነት አሳውቆ የመክፈል ሁኔታ (7%)
11) የሃገር ውስጥ ገቢ የኦዲት ግኝት መጠን (8%)
12) በዕቅድ የመመራት ባህል (3%)
13) የፀደቀ የአሰራር ስርዓት (6%)
14) የስልጠና አሰጣጥ ሁኔታ (3%)
15) የሰራተኛ ደህንነት ሁኔታ (3%)
16) የመረጃ ቴክኖሎጂ ደህንነት ሁኔታ (5%)
17) የመረጃ ቴክኖሎጂ ትስስር ሁኔታ (5%)
18) የመረጃ ቴክኖሎጂ የማስተዳደር ሁኔታ (5%)
19) የመረጃ አያያዝና ደህንነት ሁኔታ (4%)
20) የድርጅቱ ቅጥር ግቢና መጋዘን ደህንነት ሁኔታ (6%)

መ) የዕቃና የጉምሩክ አስተላላፊ

1) ባለፉት ሁለት ዓመታት የተያዘ የቀላል ጥፋት ሪከርድ (25%)
2) ዲክለር በተደረጉ ሰነዶች ላይ በተደረገ ዳግም ማጣራት የተከፈለ ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ (የገንዘብ መጠን) በመቶኛ (20%)
3) በሁለት ዓመት ዲክለር በተደረጉ ሰነዶች አማካይ የንግድ መጠን (15%)
4) ዲክለር ባደረጋቸው ሰነዶች ላይ በተደረገ ዳግም ማጣራት ልዩነት የተገኘባቸው ሰነዶች (በሰነድ ብዛት) በመቶኛ (10%)
5) የሚያስተናግዳቸው ደንበኞች የስራ ዘርፍ (የአምራች፣ ላኪ) (10%)
6) በሃገር ውስጥ ገቢ ዓመታዊ ግብርን በወቅቱ መክፈል (10%)
7) በሃገር ውስጥ ገቢ ያለው የስጋት ደረጃ (10%)

ከላይ የተዘረዘሩት እያንዳንዱ የመመዘኛ መስፈርቶች በተሰጠው ክብደት ተደምሮ ድርጅቱ በሚያገኘው ውጤት መሰረት 75% እና በላይ ከሆነ በተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ፕሮግራም የሚታቀፍ ይሆናል፡፡

3.10 **የፕሮግራሙ ተጠቃሚነት ዕውቅና ስለመስጠት**

ለፕሮግራሙ ተጠቃሚ ድርጅቶች የሚሰጣቸው የዕውቅና ምስክር ወረቀት ይዘት በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚዘጋጅ ሆኖ የሚከተሉት መረጃዎችን ያካተተ ይሆናል፡፡

ሀ) የመብቱ ተጠቃሚነት ሰርተፊኬት ቁጥር
ለ) ሰርተፊኬቱ የተሰጠበት ቀን
ሐ) የድርጅቱ ስም
መ) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/
ሠ) አገልግሎቱ የሚያበቃበት ቀን ናቸው፡፡

የመብቱ ተጠቃሚ በመሆናቸው አገልግሎት በሚያገኙባቸው የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች እና በሁሉም የመንግስት እና ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የቅድሚያ አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችል አንድ መታወቂያ እንዲያገኙ የሚሰጣቸው ሆኖ በመታወቂያው ላይ ጉምሩክን ጨምሮ ከሁሉም የመንግስት ተቋማት የሚያገኟቸውን ልዩ አገልግሎቶች በዝርዝር የያዘ ይሆናል፡፡

# ክፍል አራት

## 4. የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች መብትና ግዴታ

### 4.1 አስመጪ፣ አስመጪና ላኪ፣ አስመጪና አምራች እና ላኪ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች የሚያገኟቸው ልዩ መብቶች

ሀ) የድህረ ክፍያ አገልግሎት (Deferred payment) የማግኘት፤

ለ) ወደ ሃገር ውስጥ ለሚያስገባው እቃ ለትራንዚት በደብዳቤ ዋስትና የመስተናገድ፤

ሐ) ቀለል ያለ የጉምሩክ አሠራር (Simplified Declarations) የመጠቀም፤

መ) ዕቃዎችን በተደጋጋሚ የሚልክ ወይም የሚያስመጣ ከሆነ ለሁሉም ወጪና ገቢ ዕቃ የተጠቃለለ አንድ ዲክላራሲዮን ብቻ የማቅረብ፤

ሠ) የልዩ አገልግሎት መስጫ መስኮት የመጠቀም፤

ረ) በየትኛውም የጉምሩክ አገልግሎት ቅድሚያ የማግኘት፤

ሰ) ለአካላዊ ፍተሻ ለሚመረጡ ዕቃዎች በድርጅቱ መጋዘን የመፈተሽ፤

ሸ) ቅድመ ዕቃ አወጣጥ አገልግሎት (Pre-Arrival Clerance) የመስተናገድ፤

ቀ) በደብዳቤ ዋስትና በኮፒ ሰነድ መስተናገድ፤

በ) በሌሎች መንግስታዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ቅድሚያ አገልግሎት እንዲያገኙ ድጋፍ ማድረግ፤

ተ) ለላኪዎች ዕቃቸው ጉምሩክ መምጣት ሳያስፈልገው በቀጥታ ከመጋዘናቸው እንዲልክ ይደረጋል፤

ቸ) የጉምሩክ ኮሚሽን የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ አርማ (Logo) የመጠቀም፤ ቅድሚያ የተመላሽ መብት፤

ነ) ለሚያቀርቡት ማናቸውም የጉምሩክ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች በቅድሚያ የመገልገል መብት

ኘ) በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ የመስተናገድ፤

አ) የጉምሩክ መጋዘን ፈቃዶችን ቅድሚያ የማግኘትና የመስተናገድ፤

### 4.2 የዕቃ አስተላላፊና የጉምሩክ አስተላላፊ ልዩ መብቶች

ሀ) በማንኛውም የጉምሩክ አገልግሎት ቅድሚያ የማግኘት፤

ለ) ከጉምሩክ አሰራር ጋር በተያያዘ ህጎች ሲወጡ ከመጽደቃቸው በፊት የመሳተፍ፤ ከፀደቁ በኋላ በቋሚነት እንዲደርሳቸው ማድረግ፤

ሐ) ለሚያቀርቡት ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ቅድሚያ የመገልገል መብት፤

የኢትዮጵያ የጉምሩክ ኮሚሽን ... ቁጥር 1 No.1 Ethiopia Customs Comm... Recordes Documentation

መ) ማናቸውም የጉምሩክ መረጃዎችን በፍጥነት የማግኘት መብት፤

## 4.3 የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ድርጅት ግዴታ

በተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም የታቀፈ ድርጅት የሚከተሉትን ግዴታዎች ሊወጣ ይገባል፡፡

ሀ) የገቢም ሆነ ወጪ ዕቃዎች ለፍተሻ እና ሰነድ ምርመራ ሲመረጡ ተባባሪ መሆን፤

ለ) በፕሮግራሙ ተጠቃሚ በመሆኑ ምክንያት በዚህ አሰራርና በሌሎች ህጎች የተሰጠውን መብት በአግባቡ መጠቀም፤

ሐ) በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ሂደት ተባባሪ መሆንና አስፈላጊ ሰነዶችን ማቅረብ፤

መ) በጉምሩክ የሚፈለግባቸውን ቀረጥና ታክስ በታማኝነት የመክፈል፤

ሠ) በሃገር ውስጥ ገቢ የሚፈለግባቸውን ክፍያ በወቅቱ እና በትክክል አሳውቆ መክፈል፤

ረ) ከፕሮግራሙ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎች ሲጠየቅ ለኮሚሽኑ በመስጠት ተባባሪ መሆን፤

ሰ) ከሎጅስቲክሱ ጋር የተያያዘ የውስጥ የአሰራርና የሲስተም ለውጥ ሲያደረግ በወቅቱ ለኮሚሽኑ ማሳወቅ፤

ሸ) አዳዲስ ማስፋፊያዎች ሲያደርግ ወይም በተለያየ ምክንያት ቢዘጋ ለኮሚሽኑ ማሳወቅ፤

ቀ) የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ለመሆን በተፈራረመው የስምምነት ሰነድ መሰረት የፕሮግራሙ ተጠቃሚነት ሰርተፊከቱ የአገልግሎት ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት የእድሳት ጥያቄ ለኮሚሽኑ ማቅረብ፤

በ) የስራ እና የቦታ ለውጥ ሲያደርግ በወቅቱ ለኮሚሽኑ ማሳወቅ፤

ተ) የስነ ምግባር ችግር ያለባቸውን ሰራተኞች እየለየ እንደ ጥፋቱ መጠን እርምጃ መውሰድ እና ለኮሚሽኑ የማሳወቅ፤

ቸ) ከሎጂስቲክስ ጋር በተያያዘ የሚገጥመውን ችግር በየወቅቱ ሪፖርት ማድረግ እና ችግሮችን በጋራ ለመፍታት ዝግጁ መሆን ይጠበቅበታል፡፡

## 4.4 ኮሚሽኑ በተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ፕሮግራም ተጠቃሚ ጋር ስለሚኖረው የግንኙነት መርህ

የአለማቀፍ ንግድ ሰንሰለት ውስብስብነት ለመቀነስና የሎጀስቲክስ ደህንነት ለመጠበቅ እንዲሁም ንግዱን ለማሳለጥ የጉምሩክና የንግዱ ማህበረሰብ አጋርነት ወሳኝ ነው፡፡ ጉምሩክ ኮሚሽን ከንግዱ ማህበረሰብ ጋር አጋርነቱን ከሚያጠናክርባቸው አሰራሮች መካከል

የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም አንዱ ነው፡፡ በዚህ ፕሮግራም የሚታቀፉ ድርጅቶች አጠቃላይ ውስጣዊ የሎጅስቲክስ አሰራራቸው እና ፖሊሲያቸው በገቢ እና በወጪ ዕቃዎች ላይ ጠንካራ ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችልና ከጉምሩክ ጋር የሚደረገው ግንኙነት ለጋራ ጥቅም ሲባል በትብብርና እርስበርስ በመተማመን ላይ የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል፡፡

የዓለም ጉምሩኮች ድርጅት የጉምሩክ አስተዳደር ከተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ጋር የሚኖረው የሁለትዮሽ ግንኙነት በሚከተሉት ስድስት መርሆች መሰረት መመራት እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡

እነዚህም፡-

1. አጋርነት (Partnership)
2. ደህንነት (Security)
3. ስልጣን መስጠት (Authorization)
4. ቴክኖሎጂ (Technology)
5. የመረጃ ልውውጥ (Communication)
6. የንግድ ማሳለጥ (Facilitation)

# ክፍል አምስት

## 5. ተግባርና ኃላፊነት

### 5.1 የጉምሩክ ኮሚሽን ተግባርና ኃላፊነት

በኮሚሽኑ የተለያዩ የስራ ክፍሎች የሚከተሉት የቁጥጥር፣ ክትትልና የመረጃ ልውውጥ ተግባራት የማከናወን ኃላፊነት አለባቸው፡፡

### 5.2 የንግድ ገቢ ዕቃ አወጣጥ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) ፕሮግራሙን ለማሳደግ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም በፕሮግራሙ ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር፤

ለ) ለፕሮግራሙ ያመለከተ አዲስ ድርጅት የኦዲት ሂደቱን በመከተልና ኦዲት በማከናወን ብቁ ሆኖ ሲገኝ በፕሮግራሙ እንዲታቀፍ ለኮሚሽኑ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤ ውሳኔ ሲያገኝ የመግባቢያ ሰነድ እንዲፈረም ያደርጋል፤

ሐ) ለነባር ድርጅት በዚህ አሰራር መሰረት የእድሳት ኦዲት በማድረግ ለኮሚሽኑ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤ ውሳኔ ሲያገኝ የመግባቢያ ሰነድ እንዲፈረም ያደርጋል፤

መ) በኮሚሽኑ እና በአገልግሎት ሰጪ የመንግስት ተቋማት ድርጅት ማግኘት ያለበትን ጥቅም እያገኘ ስለመሆኑ ያረጋግጣል፤

ሠ) ለፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች እና ለውስጥ ሰራተኞች ስልጠና በመስጠት፣ ከፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች ልምዶችን በመቀመር እና አለም አቀፍ ልምዶችን ወደ ሀገራችን በማምጣት ፕሮግራሙን ያሳድጋል፤

ረ) በፕሮግራሙ ለታቀፉ ድርጅቶች ተገቢውን ቁጥጥር ለማድረግ እና በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ ተወዳዳሪነታቸውን ለማሳደግ የሚያስችል ጠንካራ የውስጥ አሰራር እንዲዘረጉ ለማድረግ ምክረ-ሃሳብ ይለግሳል፤

ሰ) በፕሮግራሙ የታቀፈ ድርጅት የተሰጠው መብት አላግባብ መጠቀሙን ሲያረጋግጥ እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ የውሳኔ ሀሳብ ለኮሚሽኑ ያቀርባል፤ በኮሚሽኑ በሚሰጥ ውሳኔ መሰረት ለድርጅቱ እና ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፤

ሸ) በሚስተናገድባቸው የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች እና ሃገር ውስጥ ገቢ የሚያጋጥመውን ችግሮች በተቀላጠፈ አሰራር ጊዚያዊና ዘላቂ መፍትሔ በመስጠት እገዛ ያደርጋል፡፡

ቀ) ለፕሮግራሙ ተጠቃሚ ድርጅት በጉምሩክ በኩል የሚገጥመውን ችግሮች በጋራ ለመፍታት የመወያያ መድረክ ያዘጋጃል፤

በ) በፕሮግራሙ የታቀፈ ድርጅት በሌሎች መንግስታዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚያጋጥመውን የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች ለመፍታት ድጋፍ ያደርጋል፤

ተ) በአሰራርና በህግ ተገዥነት ምርጥ ተሞክሮ ያላቸውን ድርጅቶች ልምድ በመቀመር ለሌሎች የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ድርጅቶች ያካፍላል፤

ቸ) የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች ዝርዝር አደራጅቶ በመያዝ በየጊዜው ወቅታዊ ያደርጋል፤

## 5.3 **የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት**

የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ድርጅት በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ የሚስተናገድ በመሆኑ የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የስራ ክፍል የቁጥጥሩ ሚዛን በማስጠበቅ ረገድ እጅግ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም የስራ ክፍሉ እስከ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የስራ ክፍሎች ድረስ በማስተባበር የሚከተሉት ተግባራት ያከናውናል፦

ሀ) የድህረ ዕቃ አወጣጥ የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ድርጅት ግዴታውን እየተወጣ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ትኩረት ሰጥቶ በዕቅድ በማካተት ኦዲት ያደርጋል፤

ለ) በኦዲት ሂደት የሚገኘው ውጤት ለንግድ ገቢ ዕቃ አወጣጥ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት በደብዳቤ ያሳውቃል፤

ሐ) የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ድርጅት ቀረጥና ታክስ በታማኝነት እንዲከፍል ለማድረግ ከንግድ ገቢ ዕቃ አወጣጥ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ጋር በጋራ መስራት፤

## 5.4 **የህግ ተገዥነት እና ስጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት**

ሀ) በተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ፕሮግራም ለመታቀፍ የሚያመለክት ድርጅት በጉምሩክ የህግ ተገዥነት የኋላ ታሪክ መረጃ ለንግድ ገቢ ዕቃ አወጣጥ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት መስጠት፤

ለ) የኦዲት ሂደቱን አልፎ በፕሮግራሙ እንዲታቀፍ ማረጋገጫ የተሰጠው ድርጅት ወደ አገር ውስጥ ለሚያስገባውም ሆነ ወደ ውጪ ለሚልከው ዕቃ በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ እንዲስተናገድ ማድረግ፤ ሆኖም ግን በተመረጠ አግባብ የስጋት ደረጃው ሊቀየር ይችላል፡፡

ሐ) በፕሮግራሙ የታቀፈ ድርጅት ከገቢና ወጪ ዕቃዎች ጋር በተያያዘ በማንኛውም ጊዜ ጥፋቶች ሲኖሩ በወቅቱ ለንግድ ገቢ ዕቃ አወጣጥ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ማሳወቅ፤

መ) የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ድርጅት የጉምሩክ ህግ ተገዢነቱን ለማጎልበት ከንግድ ገቢ ዕቃ አወጣጥ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ጋር በጋራ መስራት፤

## 5.5 **የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት**

ሀ) በፕሮግራሙ ለታቀፈ ድርጅት የተቀላጠፈ አገልግሎት ማግኘቱን ማረጋገጥ፤

ለ) በፕሮግራሙ የታቀፈ ድርጅት የሚስተናገድበት የእቃ አወጣጥ የስራ ክፍል ማዘጋጀት፤

ሐ) በፕሮግራሙ ተጠቃሚ ላይ ችግሮች ሲስተዋሉ መረጃው ለዋናው መ/ቤት ለንግድ ገቢ ዕቃ አወጣጥ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ማሳወቅ፤

## ክፍል ስድስት

## 6. የዕውቅና ሰርተፊኬት ስለማደስ ፣ ማገድ እና ስረዛ

### 6.1 ስለማደስ

ሀ) ማንኛውም የፕሮግራሙ ተጠቃሚ የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ 2 ዓመት ሲሞላው በዚህ የአሰራር ስርዓት መሰረት ኦዲት ተደርጎ የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀቱ መታደስ አለበት፤

ለ) በአሰራርና ህግ ተገዥነት የኦዲት ሂደት በፕሮግራሙ ለመቀጠል ብቁ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

### 6.2 ስለማገድ

ሀ) የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ድርጅት የተጠቃሚነት ጊዜው ያልተጠናቀቀ ቢሆንም በማንኛውም ጊዜ ግኝት የተገኘበት እንደሆነና ግኝቱ ድርጅቱ በራሱ ተነሳሽነት ዲክሌር አድርጎ ከከፈለዉ ቀረጥና ታክስ ወይም በሀገር ውስጥ ገቢ ኦዲት ተደርጎ በራሱ አሳውቆ ከከፈለው ሲነፃፀር ከ5% በላይ የሆነ የቀረጥና ታክስ ግኝት የተገኘበት እንደሆነ እና በየደረጃው ባለ አቤቱታ አጣሪስራ ክፍሎች እና ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔ አግኝቶ እንዲከፍል የፀናበት ከሆነ ከፕሮግራሙ እንዲታገድ ይደረጋል፡፡

ለ) በጉምሩክና ታክስ ማጭበርበር ወንጀል ተጠርጥሮ ምርመራ እየተከናወነበት ከሆነ፤

ሐ) የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ድርጅት በሌሎች የሀገሪቱ ህጎች ጥፋት በመፈጸም ተጠርጥሮ የክስ ሂደት ላይ ካለ ነጻ መሆኑ አግባብነት ባለው አካል እስኪረጋገጥ ድረስ ይታገዳል፡፡

መ) ከላይ ሀ፣ ለ እና ሐ ላይ የተገለፁት ቢኖርም የመጨረሻ ውሳኔ በሚሰጠው የፍርድ አካል ጥፋቱ ከተሻረ ከመታገዱ በፊት የነበረው የፕሮግራሙ ተጠቃሚነት ይቀጥላል፡፡

ሠ) ኮሚሽኑ የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ድርጅት ከፕሮግራሙ ሊያሳግድ የሚችል ምክንያት መኖሩን ካመነ በኮሚሽነሩ በሚሰጥ ውሳኔ ድርጅቱ በማንኛውም ጊዜ ታግዶ ሊጣራ ይችላል፡፡

6.3 **ስለመሰረዝ**

ሀ) የአሰራርና የህግ ተገዥነት ኦዲት ተደርጎ በፕሮግራሙ ሊያስቀጥለው የሚችል መመዘኛ መስፈርቱን ካላሟላ፤

ለ) የተሰጠውን መብት አላግባብ እየተጠቀመ ስለመሆኑ ሲረጋገጥ፤

ሐ) በጉምሩክም ሆነ በሃገር ውስጥ ገቢ በሚከናወን የኦዲት ግኝት ድርጅቱ በራስ ተነሳሽነት ከከፈለው ከ5 በመቶ በላይ ሆኖ የመጨረሻ ውሳኔ በሚሰጠው የፍርድ አካል የፀና ከሆነ፤

መ) ኮሚሽኑ በያዘው የኦዲት ፕሮግራም መሰረት እድሳት ለማድረግ የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን ኦዲት ከተደረገ ጊዜ ጀምሮ በ10 የስራ ቀን ጊዜ ወይም በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የተጠየቁ ማስረጃዎች ማቅረብ አለመቻሉ ታምኖበት የሚሰጥ ተጨማሪ የጊዜ ገደብ ውስጥ ማቅረብ ካልቻለ፤

ሠ) ድርጅቱ በተለያየ ምክንያት ከተዘጋ፣ በፕሮግራሙ ተጠቃሚነት ለመቀጠል ፈቃደኛ ካልሆነ፣

ረ) የጉምሩክ አስተላላፊ ድርጅት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አምስት ቀላል ጥፋት ወይም ሁለት ከባድ ጥፋት ከፈፀመ ከፕሮግራሙ ይሰረዛል፡፡

ሰ) ድርጅቱ የታገደ ከሆነ የእግዱን መነሻ በማስተካከል በ6 ወር ውስጥ እግዱ ያልተነሳ ከሆነ ይሰረዛል፤

ሸ) ኮሚሽኑ የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ድርጅት ከፕሮግራሙ ሊያሰርዝ የሚችል ምክንያት መኖሩን ካመነ በኮሚሽነሩ በሚሰጥ ውሳኔ ድርጅቱ በማንኛውም ጊዜ ሊሰረዝ ይችላል፤

ቀ) የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ድርጅት በመደበኛ ህግ የሚያስጠይቅ ጥፋት ፈፅሞ ከተገኘ ከፕሮግራሙ መሰረዙ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሚመለከተው አካል ለተጨማሪ ምርመራ ሊላክ ይችላል፤

## ክፍል ሰባት

## 7. ልዩ ልዩ ሁኔታ እና የአገልግሎት መስጫ ጊዜ

### 7.1 ልዩ ልዩ ሁኔታዎች

ሀ) በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ጥያቄ ያቀረበ ድርጅት የቅድመ ኦዲት መስፈርቶችን ባለማሟላቱ ተቀባይነት ካላገኘ ወይም የአሰራርና ህግ ተገዥነት ኦዲት ተደርጎ በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ብቁ ካልሆነ ያለበትን ክፍተቶች በማስተካከል ከስድስት(6) ወር በኋላ እንደ አዲስ በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡

ለ) የእድሳት ኦዲት ተደርጎ ወይም በተለያዩ ግኝቶች/ማስረጃ ምክንያት ከፕሮግራሙ የተሰረዘ ድርጅት ከአንድ ዓመት በኋላ በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡

ሐ) ከአንድ በላይ የስራ ዘርፍ ለተሰማራ ድርጅት ከተሰማራባቸው በዝቅተኛው መመዘኛ መስፈርት እንዲመዘን ይደረጋል፡፡

መ) የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ድርጅት ለእግዱ ወይምለ መሰረዙ ምክንያት የሆነው ከድርጅቱ ውጭ በሆነ አካል ወይም ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ የታመነበት እንደሆነ በሚሽኑ በሚሰጥ ውሳኔ እግዱ ወይም ስረዛው ሊነሳ ይችላል፡፡

## 7.2 ጥቅል የአገልግሎት መስጫ ጊዜ

| ተ ቁ | የሚከናወኑ ተግባራት | ቅድመ ሁኔታ | የሚወስደው ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 1 | በተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም ለመታቀፍ የሚቀርብ ማመልከቻና የራስ መገምገሚያ/Self-evaluation form/ ቅፅ ተቀብሎ ማረጋገጥ፡፡ | ◆ በድርጅቱ የተፃፈ ደብዳቤና ተሞልቶ የቀረበ የማመልከቻና የራስ መገምገሚያ ቅፅ፣<br>◆ ሌሎች ለቅድመ ኦዲት መስፈርት የሚያስፈልጉ መረጃዎች፣ | 15 ደቂቃ |
| 2 | የራስ መገምገሚያ ያለፉ ድርጅቶች የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት የድርጅቱን ሙሉ የአሰራርና የህግ ተገዢነት ኦዲት ማከናወን፤ | ◆ የተሟላ ማመልከቻ እና የራስ መገምገሚያ ቅፅ፤<br>◆ የድርጅቱ የጉምሩክና የአገር ውስጥ ታክስ የህግ ተገዥነት ቅድመ ታሪክ፤<br>◆ የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሳሾች የህግ ተገዥነት ኦዲት ዝርዝር መስፈርት፤ | 10 ቀን |
| 3 | የኦዲት ማጠቃለያ ሪፖርት ማዘጋጀትና ከድርጅቱ ጋር የመውጫ ውይይት ማድረግ፤ | ◆ ከድርጅቱ ማመልከቻ ጀምሮ በኦዲት ሂደት የተገኙ ግብዓቶች በሙሉ፤<br>◆ የተዘጋጀ የመጀመሪያ ረቂቅ የኦዲት ሪፖርት መኖር፤ | 3 ቀን |
| 4 | በኦዲት ሪፖርቱ መሰረት ለሚያሟሉ ድርጅቶች ይህንኑ በደብዳቤ መግለፅ፤ ለሚያሟሉ ድርጅቶች የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም የዕውቅና ሰርተፊኬት መስጠት፤ | ◆ የአሰራር፤ የህግ ተገዢነት እና የሲስተም ኦዲት ሪፖርት፤<br>የጋራ ስምምነት ሰነድ /Memorandom of Understanding፤ | 2 ቀን |

# ክፍል ስምንት

## 8. ተቀጽላ

### 8.1 ተቀጽላ አንድ (1)

| | | |
|---|---|---|
| 1.የአመልካች ድርጅት ስም | | ለመ/ቤቱ ሥራ ብቻ<br>ቀን፡<br>ቁጥር፡ |
| 2. የአመልካች ድርጅት ህጋዊ መሰረት/ ደረጃ | | 3. ድርጅቱ የተቋቋመበት ጊዜ |
| 4. ድርጅቱ የተቋቋመበት ቦታ | | |
| 5. የደርጅቱ ዋና ሥራ መገኛ ቦታ | | |
| 6. የተጠሪ (ስም፣ ስ.ቁ፤ የፋክስ.ቁ እና ኢሜይል) | | 7. የድርጅቱ አድራሻ (ስ.ቁ፤ የፋክስ.ቁ እና ኢሜይል) |
| 8. የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር | | 9. የታክስ መለያ ቁጥር |
| 11.የተሰማራበት የሥራ ዘርፍ | 12. ቀድሞ የተሰጠ የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ/ የጉምሩክ ልዩ አገልግሎት ተጠቃሚነት. አለ/የለም.............<br>የሰርትፊኬት ቁጥር ይጠቀስ (ያለ ከሆነ)............................... | |
| 13. ግብር የሚከፍልበት ቅ/ጽ/ቤት | | 14. የሚስተናገድባቸው የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች |

15. የአባሪዎች ብዛት..........................

16. ከላይ የተገለጹ መረጃች በሙሉ ትክክል መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ.

ፊርማ.........................................................  ቀን...............................................

ሥም...........................................................  ኃላፊነት.........................................

## ተቀጽላ ሁለት(2)

ሀ. የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም የህግ ተገዥነትና የውስጥ የአሰራር ስርዓት ኦዲት ጥቅል የመመዘኛ መስፈርቶችና ዝርዝር የመለኪያ ነጥቦች

1. ለሃገር ኢኮኖሚ የሚያደርገው አስተዋፅኦ ....(15)
    - ሀ. የተከፈለ አማካይ የቀረጥና ታክስ መጠን ....6
    - ለ. የተከፈለ አማካይ የግብር መጠን ....6
    - ሐ. የፈጠረው የስራ እድል ....3
2. የፋይናንስ ቀጣይነት ....(10)
    - ሀ. ዕዳውን ለመክፈል ያለው አቅም....4
    - ለ. ማካይ የሽያጭ መጠን ....3
    - ሐ. አማካይ የትርፍ መጠን ....3
3. የህግ ተገዥነት ታሪክ ....(35)
    - 3.1. በጉምሩክ የህግ ተገዥነት ታሪክ....20
        - ሀ. በጉምሩክ ያለው የኦዲት ግኝት መጠን....8
        - ለ. በጉምሩክ ስነ ስርዓት ሂደት እቃና ሰነድ በዳግም ፍተሻ የግኝት መጠን ....8
        - ሐ. የጉምሩክ ወኪሉ የህግ ተገዥነት ታሪክ ....4
    - 3.2. በሃገር ውስጥ ገቢ የህግ ተገዥነት ታሪክ....15
        - ሀ. ግብርን በወቅቱ እና በፈቃደኝነት አሳውቆ መክፈል ....7
        - ለ. የኦዲት ግኝት መጠን....8
4. የገቢና ወጪ እቃዎች የሎጀስቲክስና ሃብት አመራር ስርዓት ....(15)
    - ሀ. የፀደቀ የአሰራር ስርዓት....6
    - ለ. በእቅድ የመመራት ባህል ....3
    - ሐ. ስልጠና አሰጣጥ ሁኔታ ....3
    - መ. የሰራተኛ ደህንነት ....3
5. የመረጃ ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ....(15)
    - ሀ. የመረጃ ቴክኖሎጂ ደህንነት ሁኔታ ....5
    - ለ. የመረጃ ቴክኖሎጂ ትስስር ሁኔታ ....5
    - ሐ. የመረጃ ቴክኖሎጂ የማስተዳደር ሁኔታ ....5
6. የደህንነት መስፈርቶች ....(10)
    - ሀ. የድርጅቱ ቅጥር ግቢ እና የመጋዘን ደህንነት ሁኔታ ....6
    - ለ. የመረጃ አያያዝና ደህንነት ሁኔታ ....4

| ተ.ቁ | ጥቅል የመመዘኛ መስፈርቶችና ነጥብ መስጫ መለኪያዎች | ለመለኪያው የተሰጠ ነጥብ |
|---|---|---|
| 1 | ለሃገር ኢኮኖሚ ያደረገው አስተዋፅኦ | 15% |
| 1.1 | በትክክል የተከፈለ አማካይ የቀረጥና ታክስ መጠን | 6% |
| ሀ | ያለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት የተከፈለ የቀረጥና ታክስ መጠን ከ150 ሚሊዮን ብር በላይ | 6 |
| ለ | ያለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት የተከፈለ የቀረጥና ታክስ መጠን ከ100 ሚሊዮን ብር እስከ 149.9 ሚሊዮን ብር | 5 |
| ሐ | ያለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት የተከፈለ የቀረጥና ታክስ መጠን ከ75 ሚሊዮን ብር እስከ 99.9 ሚሊዮን ብር | 4 |
| መ | ያለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት የተከፈለ የቀረጥና ታክስ መጠን ከ50 ሚሊዮን ብር እስከ 74.99 ሚሊዮን ብር | 3 |
| 1.1 | ድርጅቱ አምራች ወይም የቀረጥ ነፃ እና ሌሎች ማበረታቻዎች ተጠቃሚ ከሆነ | 6% |
| ሀ | የኢንቨስትመንት መጠን ከ400 ሚሊዮን ብር በላይ | 6 |
| ለ | የኢንቨስትመንት መጠን ከ250 እስከ 399.99 ሚሊዮን ብር | 5 |
| ሐ | የኢንቨስትመንት መጠን ከ100 እስከ 249.99 ሚሊዮን ብር | 4 |
| መ | የኢንቨስትመንት መጠን ከ50 እስከ 99.99 ሚሊዮን ብር | 3 |
| 1.2 | በወቅቱና በትክክል የተከፈለ አማካይ የሀገር ውስጥ የግብር መጠን | 6% |
| ሀ | ያለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት የተከፈለ የግብር መጠን ከ50 ሚሊዮን ብር በላይ | 6 |
| ለ | ያለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት የተከፈለ የግብር መጠን ከ35 እስከ 49.9 ሚሊዮን ብር | 5 |
| ሐ | ያለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት የተከፈለ የግብር መጠን ከ20 እስከ 34.9 ሚሊዮን ብር | 4 |
| መ | ያለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት የተከፈለ የግብር መጠን ከ10 እስከ 19.9 ሚሊዮን ብር | 3 |
| ሠ | ያለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት የተከፈለ የግብር መጠን ከ5 እስከ 9.99 ሚሊዮን ብር | 2 |
| | ድርጅቱ የግብር እፎይታ ላይ ከሆነ | |
| ሀ | የኢንቨስትመንት መጠን ከ400 ሚሊዮን ብር በላይ | 6 |
| ለ | የኢንቨስትመንት መጠን ከ250 እስከ 399.99 ሚሊዮን ብር | 5 |
| ሐ | የኢንቨስትመንት መጠን ከ100 እስከ 249.99 ሚሊዮን ብር | 4 |
| መ | የኢንቨስትመንት መጠን ከ50 እስከ 99.99 ሚሊዮን ብር | 3 |
| 1.3 | የፈጠረው የስራ እድል | |
| 1.3.1 | ለአምራች | |

| | | |
|---|---|---|
| ሀ | የቋሚና ኮንትራት ሰራተኞች ብዛት 250 እና በላይ | 3 |
| ለ | የቋሚና ኮንትራት ሰራተኞች ብዛት ከ100 እስከ 249 | 2 |
| ሐ | የቋሚና ኮንትራት ሰራተኞች ብዛት ከ100 በታች | 1 |
| 1.3.2 | አስመጪ/ላኪ | |
| ሀ | የቋሚና ኮንትራት ሰራተኞች ብዛት 100 እና በላይ | 3 |
| ለ | የቋሚና ኮንትራት ሰራተኞች ብዛት ከ70 እስከ 99 | 2 |
| ሐ | የቋሚና ኮንትራት ሰራተኞች ብዛት ከ70 በታች | 1 |
| 2 | የፋይናንስ ቀጣይነት | 10% |
| 2.1 | እዳውን ለመክፈል ያለው አቅም (የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ላይ ላልሆነ) | 4% |
| ሀ | ወቅታዊ እዳውን ለመክፈል ያለው አቅም (Current ratio) 1.3 እና በላይ | 4 |
| ለ | ወቅታዊ እዳውን ለመክፈል ያለው አቅም (Current ratio) ከ1.0 — 1.29 | 3 |
| 2.2 | ያለፉት ተከታታይ ሁለት ዓመታት አማካይ ሽያጭ | 3% |
| አስመጪ | አማካይ ሽያጭ ከ800 ሚሊዮን ብር በላይ | 3 |
| | አማካይ ሽያጭ ከ400 እስከ 799 ሚሊዮን ብር | 2 |
| ላኪ | አማካይ የውጭ ምንዛሬ መጠን ከ10 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ያስገኘ | 3 |
| | ከ5 እስከ 9.9 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ያስገኘ | 2 |
| አምራች | አማካይ ሽያጭ ከ500 ሚሊዮን ብር በላይ | 3 |
| | አማካይ ሽያጭ ከ300 እስከ 499.99 ሚሊዮን ብር | 2 |
| 2.3 | ያለፉት ተከታታይ ሁለት ዓመታት አማካይ የትርፍ መጠን | 3% |
| ሀ | የትርፍ መጠን 150 ሚሊዮን ብር በላይ | 3 |
| ለ | የትርፍ መጠን ከ100 -149.99 ሚሊዮን ብር | 2 |
| ሐ | የትርፍ መጠን ከ50 እስከ 99.99 ሚሊዮን ብር | 1 |
| | ድርጅቱ የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ላይ ከሆነ | |
| ሀ | የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ መጠን ከ400 ሚሊዮን ብር በላይ | 3 |
| ለ | የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ መጠን ከ300 - 399.9 ሚሊዮን ብር | 2 |
| ሐ | የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ መጠን ከ200 እስከ 299.99 ሚሊዮን | 1 |

| | | |
|---|---|---|
| 3 | የህግ ተገዥነት ታሪክ ሁኔታ | 35% |
| 3.1 | በጉምሩክ የህግ ተገዥነት ታሪክ | 20% |
| 3.1.1 | በድህረ እቃ አወጣጥ የኦዲት ግኝት መጠን | 8 |
| ሀ | ኦዲት ተደርጎ የኦዲት ግኝት የሌለበት | 8 |
| ለ | ኦዲት ተደርጎ የኦዲት ግኝት መጠን እስከ 1.5% | 7 |
| ሐ | በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ጥያቄ ባቀረበበት በጀት ዓመት ኦዲት ያልተደረገ እና የስጋት ደረጃው ዝቅተኛ/መካከለኛ ከሆነ | 6 |
| መ | ኦዲት ተደርጎ የኦዲት ግኝት መጠን ከ1.51% - 3% | 5 |
| ሠ | በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ጥያቄ ባቀረበበት በጀት ዓመት ኦዲት ያልተደረገ እና የስጋት ደረጃው ከፍተኛ ከሆነ | 4 |
| ረ | ኦዲት ተደርጎ የኦዲት ግኝት መጠን ከ3.1% - 5% | 3 |
| 3.1.2 | በጉምሩክ ስነ ስርዓት ሂደት የተከፈለ ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ መጠን | 8 |
| ሀ | በተደረገው የሰነድ/የእቃ ማጣራት ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ ክፍያ ከሌለው | 8 |
| ለ | በተደረገው የሰነድ/የእቃ ማጣራት ተጨማሪ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ክፍያ መጠን እስከ 1.5% | 7 |
| ሐ | በተደረገው የሰነድ/የእቃ ማጣራት ተጨማሪ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ክፍያ መጠን ከ1.51% - 3% | 6 |
| መ | በተደረገው የሰነድ/የእቃ ማጣራት ተጨማሪ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ክፍያ መጠን ከ3.1% - 5% | 5 |
| 3.1.3 | የወኪሉ የህግ ተገዥነት ታሪክ | 4% |
| ሀ | የወኪሉ የስጋት ደረጃ ዝቅተኛ | 4 |
| ለ | የወኪሉ የስጋት ደረጃ መካከለኛ | 3 |
| ሐ | የወኪሉ የስጋት ደረጃ ከፍተኛ | 1 |
| 3.2 | በሃገር ውስጥ ገቢ የህግ ተገዥነት ታሪክ | 15 |
| 3.2.1 | ዓመታዊ ግብርን በወቅቱ እና በፈቃደኝነት አሳውቆ የመክፈል ሁኔታ | 7 |
| ሀ | ዓመታዊ ግብሩን በፈቃደኝነትና በወቅቱ የሚከፍል | 7 |
| ለ | ዓመታዊ ግብሩን በወቅቱ ባለመክፈሉ በቅጣት የተስተናገደ ከሆነ | 4 |
| 3.2.2 | የኦዲት ግኝት መጠን ከከፈለው ዓመታዊ ግብር አንፃር | 8 |
| ሀ | ኦዲት ተደርጎ የኦዲት ግኝት የሌለው | 8 |
| ለ | ኦዲት ተደርጎ የኦዲት ግኝት መጠን እስከ 1.5% | 7 |
| ሐ | በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ጥያቄ ባቀረበበት በጀት ዓመት ኦዲት ያልተደረገ እና የስጋት ደረጃው ዝቅተኛ ከሆነ | 6 |
| መ | የኦዲት ግኝት መጠን ከ1.51% - 3% | 5 |

| | | |
|---|---|---|
| ሠ | በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ጥያቄ ባቀረበበት በጀት ዓመት ኦዲት ያልተደረገ እና የስጋት ደረጃው ከፍተኛ ከሆነ | 4 |
| ረ | የኦዲት ግኝት መጠን ከ3.1% - 5% | 3 |
| 4 | የገቢና ወጪ እቃዎች ሎጀስቲክስና ሃብት አመራር ስርዓት | 20% |
| 4.1 | በእቅድ የመመራት ባህል | 3 |
| ሀ | የመካከለኛ ወይም ስትራቴጂክ እቅድ ያለው | 3 |
| ለ | ኦፕሬሽናል እቅድ ካለው | 2 |
| 4.2 | የፀደቀ የአሰራር ስርዓት | 6 |
| ሀ | ሁሉም የስራ ክፍሎች የአሰራር ስርዓት ካላቸው | 6 |
| ለ | የመጋዘን፣ የፋይናንስ እና የወጪ-ገቢ እቃ የስራ ክፍሎች የአሰራር ስርዓት ካላቸው | 5 |
| 4.3 | የስልጠና አሰጣጥ ሁኔታ | 3 |
| ሀ | ከሎጀስቲክስ ጋር በተያያዘ ስልጠና የወሰዱ የክፍሉ ሰራተኞች እስከ 75% | 3 |
| ለ | ከሎጀስቲክስ ጋር በተያያዘ ስልጠና የወሰዱ የክፍሉ ሰራተኞች ከ50% - 74% | 2 |
| ሐ | ከሎጀስቲክስ ጋር በተያያዘ ስልጠና የወሰዱ የክፍሉ ሰራተኞች ከ25% - 49% | 1 |
| 4.4 | የሰራተኛ ደህንነት | 3 |
| ሀ | የደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁስ ያለው፣ ለሰራተኞች የስራ ላይ ኢንሹራንስ ከተገባላቸው፣ የመጀመሪያ ደረጃ የህክምና መስጫ ቁሳቁስ ያለው | 3 |
| ለ | የደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁስ ያለው፣ ለሰራተኞች የስራ ላይ ኢንሹራንስ ከተገባላቸው | 2 |
| ሐ | የደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁስ ካለው | 1 |
| 5 | የመረጃ ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት | 15 |
| 5.1 | የመረጃ ቴክኖሎጂ ደህንነት ሁኔታ | 5 |
| ሀ | የደህንነት መጠበቂያ (Firewall) እና በሰርተፍኬት የተረጋገጠ የቫይረስ መከላከያ የሚጠቀም፣ የመረጃ ማዕከል ያለው፣ ከድርጅቱ ቅጥር ግቢ ውጭ አማራጭ የመረጃ ማዕከል (Disaster recovery back up) ካለው፣ | 5 |
| ለ | የደህንነት መጠበቂያ (Firewall) እና በሰርተፍኬት የተረጋገጠ የቫይረስ መከላከያ የሚጠቀም፣ የመረጃ ማዕከል ያለው፣ | 4 |
| ሐ | የደህንነት መጠበቂያ (Firewall) እና በሰርተፍኬት የተረጋገጠ የቫይረስ መከላከያ የሚጠቀም፣ በሃርድ ዲስክ መረጃዎችን የሚይዝ | 3 |
| 5.2 | የመረጃ ቴክኖሎጂ ትስስር ሁኔታ | 5 |
| ሀ | ሁሉም የስራ ክፍሎች የተሳሰሩ | 5 |
| ለ | የመጋዘን፣ የፋይናንስ እና የገቢ-ወጪ የስራ ክፍሎች የተሳሰሩ | 4 |
| ሐ | የመጋዘንና የፋይናንስ የስራ ክፍሎች የተሳሰሩ | 3 |

| | | |
|---|---|---|
| 5.3 | የመረጃ ቴክኖሎጂ የማስተዳደር ሁኔታ | 5 |
| ሀ | ራሱን የቻለ የመረጃ ቴክኖሎጂ የስራ ክፍል ያለው፣ በተጠቃሚዎች መካከል ግልፅ የሆነ የስራ ክፍፍል ያለው፣ | 5 |
| ለ | ቋሚ/ኮንትራት የመረጃ ቴክኖሎጂ ባለሙያ ያለው፣ በተጠቃሚዎች መካከል ግልፅ የሆነ የስራ ክፍፍል ያለው፣ | 3 |
| 6 | የደህንነት መስፈርቶች | 10 |
| 6.1 | የመረጃ አያያዝና ደህንነት ሁኔታ | 4 |
| ሀ | የድርጅቱን መረጃ ከሰው ሰራሽና ከተፈጥሮ አደጋዎች ብልሽት ለመከላከል የሚያስችል ጠንካራ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ካለው | 4 |
| ለ | የድርጅቱን መረጃ ከሰው ሰራሽና ከተፈጥሮ አደጋዎች ብልሽት ለመከላከል የሚያስችል መካከለኛ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ካለው | 3 |
| ሐ | ደካማ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ካለው | 1 |
| 6.2 | የድርጅቱ ቅጥር ግቢ እና መጋዘን ደህንነት ሁኔታ | 6 |
| ሀ | የሰራተኛ መግቢያና መውጫ በር ከእቃዎች መግቢያና መውጫ በር የተለየ ከሆነ፣ በብሎኬት/በብረት/ኤሌክትሪክ የታጠረ አስተማማኝ አጥር ያለው፤ የእሳት ማጥፊያ እና የደህንነት ካሜራ ያለው | 6 |
| ለ | የራሱ በብሎኬት የታጠረ አስተማማኝ አጥር ያለው፤ የእሳት ማጥፊያ እና የደህንነት ካሜራ ያለው | 4 |

## ለ. ተጨማሪ ነጥብ (Bonus) የሚያስገኙ መለኪያዎች

| ተ.ቁ | መለኪያዎች | የሚያስገኘው ነጥብ |
|---|---|---|
| 1 | የእቃ መልቀቂያ ተሰጥቶት በራሱ መጋዘን ከደረሰ በኋላ ያልተከፈለ ቀረጥና ታክስ መኖሩን ባወቀ ጊዜ በራሱ ተነሳሽነት አሳውቆ የከፈለ | 3 |
| 2 | ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ድጋፍ የሚያደርግ ከሆነ | 2 |

## ተቀጽላ ሶስት(3)

### ሐ. የጉምሩክ አስተላላፊ የመመዘኛ መስፈርት

1) ባለፉት ሁለት ዓመታት የተያዘ የቀላል ጥፋት ሪከርድ........................................................25%
2) ዲክለር በተደረጉ ሰነዶች ላይ በተደረገ ዳግም ማጣራት የተከፈለ ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ (የገንዘብ መጠን) በመቶኛ........................................................................................................20%
3) በሁለት ዓመት ዲክለር በተደረጉ ሰነዶች አማካይ የንግድ መጠን..........................................15%
4) ዲክለር ባደረጋቸው ሰነዶች ላይ በተደረገ ዳግም ማጣራት ልዩነት የተገኘባቸው ሰነዶች(በሰነድ ብዛት) በመቶኛ..............................................................................................................10%
5) የሚያስተናግዳቸው ደንበኞች የስራ ዘርፍ (የአምራች፣ ላኪ) ................................................10%
6) በሃገር ውስጥ ገቢ ዓመታዊ ግብርን በወቅቱ መክፈል............................................................10%
7) በሃገር ውስጥ ገቢ ያለው የስጋት ደረጃ .......................................................................10%

በኢትዮጵያ የጉምሩክ ኮሚሽን
ቁጥር 1
No.1
Ethiopia Customs Com
Records Document

| ተ.ቁ | የመመዘኛ ነጥቦች | የመለኪያው ነጥብ |
|---|---|---|
| 1 | በሁለት ዓመት ውስጥ የተያዘ የቀላል ጥፋት ሪከርድ | 25% |
| ሀ | የጥፋት ሪከርድ የሌለበት | 25 |
| ለ | የጥፋት ሪከርድ ብዛት አንድ | 23 |
| ሐ | የጥፋት ሪከርድ ብዛት ከ2 - 3 | 20 |
| መ | የጥፋት ሪከርድ ብዛት ከ4 - 5 | 18 |
| 2 | ባለፉት ሁለት ዓመታት ዲክለር ባደረጋቸው ሰነዶች ላይ በተደረገ ዳግም ማጣራት የተከፈለ ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ በመቶኛ | 20% |
| ሀ | በማስተካከያ የተከፈለ ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ ክፍያ የሌለበት | 20 |
| ለ | በማስተካከያ የተከፈለ ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ ክፍያ እስከ 1.5% | 19 |
| ሐ | በማስተካከያ የተከፈለ ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ ክፍያ ከ1.51% - 3% | 18 |
| መ | በማስተካከያ የተከፈለ ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ ክፍያ ከ3.1% - 5% | 17 |
| ሠ | በማስተካከያ የተከፈለ ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ ክፍያ ከ5.1% - 8% | 15 |
| 3 | ባለፉት ሁለት ዓመታት ዲክለር ባደረጋቸው ሰነዶች ላይ በተደረገ ዳግም ማጣራት ከ5% በላይ የቀረጥና ታክስ ልዩነት የተገኘባቸው ሰነዶች በመቶኛ | 10% |
| ሀ | ልዩነት የሌለበት | 10 |
| ለ | የቀረጥና ታክስ ልዩነት የተገኘባቸው ሰነዶች ብዛት እስከ 1.5% | 9 |
| ሐ | የቀረጥና ታክስ ልዩነት የተገኘባቸው ሰነዶች ብዛት ከ1.51% - 3% | 8 |
| መ | የቀረጥና ታክስ ልዩነት የተገኘባቸው ሰነዶች ብዛት ከ3.1% - 5% | 7 |
| ሠ | የቀረጥና ታክስ ልዩነት የተገኘባቸው ሰነዶች ብዛት ከ5.1% - 8% | 6 |
| 4 | በሁለት ዓመት ዲክለር በተደረጉ ሰነዶች አማካይ የንግድ መጠን | 15% |
| 4.1 | በገንዘብ መጠን | 10% |
| ሀ | አማካይ የንግድ መጠን ከ800 ሚሊዮን ብር እና በላይ | 10 |
| ለ | አማካይ የንግድ መጠን ከ600 - 799.9 ሚሊዮን ብር | 9 |
| ሐ | አማካይ የንግድ መጠን ከ400 - 599.9 ሚሊዮን ብር | 8 |
| መ | አማካይ የንግድ መጠን ከ200 - 299.9 ሚሊዮን ብር | 7 |
| 4.2 | በሰነድ ብዛት | 5% |
| ሀ | 1000 ሰነዶች እና በላይ | 5 |

| | | |
|---|---|---|
| ለ | ከ800 - 999 ሰነዶች | 4 |
| ሐ | ከ600 - 799 ሰነዶች | 3 |
| መ | ከ400 - 599 ሰነዶች | 2 |
| 5 | የሚያስተናግዳቸው ደንበኞች የስራ ዘርፍ (የአምራች፣ ላኪ) | 10% |
| ሀ | ዲክለር ከሚያደርጋቸው ሰነዶች ውስጥ የAEO, የአምራች ወይም የላኪ ድርጅቶች ሰነድ ከ90% በላይ ከሆነ | 10 |
| ለ | ዲክለር ከሚያደርጋቸው ሰነዶች ውስጥ የAEO, የአምራች ወይም የላኪ ድርጅቶች ሰነድ ከ75% - 89.9% ከሆነ | 9 |
| ሐ | ዲክለር ከሚያደርጋቸው ሰነዶች ውስጥ የAEO, የአምራች ወይም የላኪ ድርጅቶች ሰነድ ከ50% - 74.9% ከሆነ | 8 |
| መ | ዲክለር ከሚያደርጋቸው ሰነዶች ውስጥ የAEO, የአምራች ወይም የላኪ ድርጅቶች ሰነድ ከ50% በታች ከሆነ | 7 |
| ሠ | ሙሉ በሙሉ የአስመጪ ሰነዶችን ዲክለር የሚያደርግ | 6 |
| 6 | በሃገር ውስጥ ገቢ ዓመታዊ ግብርን በወቅቱ መክፈል | 10% |
| ሀ | ዓመታዊ ግብሩን በወቅቱ የሚከፍል | 10 |
| ለ | ዓመታዊ ግብሩን በወቅቱ ባለመክፈሉ በቅጣት የተስተናገደ | 8 |
| 7 | በሃገር ውስጥ ገቢ ያለው የስጋት ደረጃ | 10% |
| ሀ | የስጋት ደረጃው ዝቅተኛ ከሆነ | 10 |
| ለ | የስጋት ደረጃው መካከለኛ ከሆነ | 8 |